ፓኖራማ ቁጥር 58

የትዝብት አድማስ

ጥር 10 2001 ዓም

## <u>አፍ የሚጎርሰውን እጅ ይመጥነዋል።</u>

ከእራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍር የተገነቡት የሰው ልጅ የሰራ አካላት፥ እየንዳንዳቸው የየራሳቸው የሥራ ድርሻና የተግባር አገልግሎት ያላቸው መሆኑን ከተጠቃሚው የበለጠ ማንም የሚያውቅው የለም። የሥራ አፈፃፀማቸውና የተግባር አገልግሎታቸው ደግሞ፥ እንዲጠቀሙት ተብለው ለተፈጠሩለት ለሰው ልጅ አገልግሎት ስለሆነ ፥ አሰራራቸው አንዱ ከሌላው ጋር እየተረዳዳና እየተቀናጀ ስለተደራጀ፥በሥርዓትና በቅንብር ሂደት ይካሄዳል። የአንዱን ተግባር ሌላው ልስራ ብሎ ቢሞክር ያበላሸው እንደሁ እንጅ፥ ጭራሽ የሚሆንለት አይሆንም። በመሆኑም እያንዳንዱ የአካል ክፍል፥ የየራሱን ምድብ ተግባር በሚገባ ለማከናወን የተፈጠረበት ባኅርይና ተግባር ይረደዋል።

እንደ ሰው ልጅ የሰራ አካላት ሥነ ሥፍጥረት አወቃቀርና አፈፃፀም ከሆነ፥ ጭንቅላት የሁሉንም የሰውነት ክፍሎች ትዕዛዝ እየሰጠ የሚያሰራቸውና የሚቆጣጠራቸው እንደሆነ ይታመናል። የሥነ ጽሁፍ ሊቃውንት ደግሞ መስማትንና ማንበብን፥ መጻፍንና መናገርን በአንድ የተግባር እመም ውስጥ ያስቀምጧቸዋል። ለመጻፍ የምትችለው፥ ማንበብን ስታዘወትርና ከማንበብ ባከማቸኸው ዕውቀትና ተመክሮ ይሆናል / ስትችል ነው እንደሚባለው ሁሉ፥ የምትናገረውም እንደዚሁ መስማትን/ ማዳመጥን ስትችል ነው ይባላል። ከባኅላዊ ልምድ በመነሳት ከመናገር ይልቅ፥ ማዳመጥ ይሻላል ቢባልም፥ የሚያውቁትን ለማካፈል ደግሞ መናገር የሚጠቅም ይሆናል። ዐይን ከፊቱ

ያለውን ለመመልከት ቢችልም፥አዙሮ ለማየት ደግሞ በግድ የአንገትን ርዳታና ትብብር ያስፈልገዋል፡፡ያ ካልተፈፀመ "አንገት የተሰራው አዙሮ ለማየት ነው፡፡" የሚባለው ይትበሃል ባላስፈለገም ነበር፡፡ ዐይን ከፊት ለፊት ሊያየው የሚችለውን ከማየት በስተቀር፥ ከግንቡ ወዲያ ያለውን ለመመልከት የተፈጥሮ ችሎታ ባይኖረውም፥በጆሮ ተባባሪነት ቢያነስ ምን እንደሚባል ሊረዳ ይችላል፡፡ ለዚህም ነው መሰል፥ " የጆሮ አጥር የለውም" የሚባለው፡፡ "በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ" መባል አስፈላጊ የሚሆንበት ወቅትና አጋጣሚ የሚከሰተው፥ ሰዎች ለአፋቸው ለከት፥ ለልሳናቸው ገደብ ሳያደርጉ እየቀሩ፥ በሌሎች ሰዎችና ተቋማት ላይ ዕውነት ያልሆነ አስተያየትና ትችት ብቻ ሳይሆን፥ ያለተቋረጠ የአሉባልታ ዘመቻ ሲያካሂዱ በሚሰሙበት ጊዜ ነው፡፡ ይህ ድርጊት የሚያስተዛዝበውና ድርጊቱን በሚፈፅመው በኩል ሊያዋርደውና ሊያቃለው የሚችለው፥ በተለይ የሃይማኖት አባቶችና የፖለቲካ መሪዎች ነን በሚሉት በኩል ሲከሰት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በበኩሉ የሞራል ሥልጣን አለን ብለው የሚመፃደቁትን ዕምነታቸውን ሁሉ መና ያደርግባቸዋል፡፡ከዚህ ደረጃ ከደረሱ በኋላ ለመፈራገጥ በሚያደርጉት የመከላከል ጥረት፥ ማጠፊያው ይቸግራቸዋል፡፡ ታዲያ ከሁሉም የሚሻለው፥ "መታፈር/ መከበር በከንፈር" የሚለውን ወርቃማ ይትበሃል አንግቦ መያዙ ይሆናል፡፡

ታላቁ የሃይማኖት መጻሕፍ "ሰውን የሚያረክሰው፥ ከአፉ የሚወጣው እንጅ፥ ወደ አፉ የሚገባው አይደለም" ብሎ እንደሚያስተምረው፥ ማንም ሰው የሚናገረውን መዝኖና መጥኖ፥ ከአፉ እንዲወጣ ካላደረገ በስተቀር፥ ሊያረክሰው የሚያስችለው መጥፎ ቃል ከአፉ ሊወጣ የሚችልበት ዕድሉ ሰፊ እንደሚሆን ሊገነዘበው ይገባል፡፡ አፍ የሚጎርሰውን እጅ ይመጥነዋል የተባለውም፥ ይህንን ለማመሳከር ሳይሆን አይቀርም፡፡ አፍ እንዳመጣ መናገርና እጅ እንደጠቀለለ መጉረስ ሁለቱም የሚያስከትሉት መከበርን ሳይሆን መዋረድን ብቻ ይሆናል፡፡ ችሎታውን፥ ልኬታውን፥ ባሕርዩንና መጠኑን በሚገባ የማያውቅ ሰው፥ ከአፉ በወጣ የሰውን ልጆች የሚያስቀይም፥ ወይም ወደ አፉ በገባ መጠን የለሽ

አሸር ባሸር ነገር የሚያበላሽ ሆኖ ይቀራል፡፡ ይህ እንዳይሆን፥ አፍ የሚጎርሰውን እጅ እየመጠነ ፥ ልሳን የሚናገረውን ከናፍር እየወሰነ የሰው ልጅ ሕይወቱን መምራት ይኖርበታል፡፡ኅብረተሰብ ኑሮውን በሠላም፥በጤና፥በሥርዓት አብኖር ተስማምቶ መኖር ካለበት፥ ይህንን ማድረግ መሠረት ነው፡፡ አፍ ለሰው ልጅ በትክክል መጠቀሚያ እንዲሆን ከተደረገ፥ በዕርግጥ የሚያበረክተው ፀጋና ጥቅም በርካታ ነው፡፡የሃይማኖት መሪዎች፥ለስብከትና ለሥነመለኮት ትምህርት ለማስታረቅና ለመመረቅ፥ መምህራን ዕውቀት ለማስተላለፍና ሥልጣኔን ለማስፋፋት፥ የፖለቲካና የጦር መሪዎች ደግሞ ለህገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ለነፃነት ዋስትና የሚሆን ንግግር ካደረጉበት፥ ጠቀሚታው ብዙ ነው፡፡

ያለመታደል ሆኖባቸው፥ ዛሬ አዲሰ አበባ በሚገኘው የምንሊክ ግቢ መሽገው ቀናቸውን በመቆጠር ላይ ያሉት የወያኔ ዘረኛ ግለሰቦች፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ በድርጊት ብቻ ሳይሆን በነባቢትም ጭምር እያሳዘኑትና እየበደሉት፥ እየሰደቡትና እያዋረዱት ለመሆናቸው ማስረጃ አምጡ የሚባል አይደለም፡፡ እኛም ራሳችን እነኝህ ባተሌዎች የተናገሩትን ሁሉ ሰብሰበን ለመፃፍ ከቶውንም አንቃጣም፡፡ ምክንያቱም “ሰድቦ ለሰዳቢ” እንዳይሆንብን ስንል ብቻ ነው፡፡አንድ ነገር ብቻ በምንም ዓይነት መንገድ ሊረሳ የማያቻል የድፍረት ንግግር መሰንዘራቸውን ግን የምንዘነጋው ከቶ አይሆንም፡፡ ይህን የድፍረትና የቅሌት አባባላቸውን በግንዛቤ ውስጥ ለማስገባት እንጅ፥ በቁስል ላይ በርበሬ ለመነስነስ ወይም ደግሞ እነርሱ በተናገሩት ምክንያት ቂም በቀሉ፥ጥላቻውና መፈራረቁ፥ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ ጭራሽ ምኞትና ፍላጎት ኖሮን አይደለም፡፡ ነገር ግን፥ የምንታገልለት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እነርሱም ቆመንለታል የሚሉትን የትግራይንም ሕዝብ ጭምር፥ታሪኩን፥ ባህሉንና ሰብዕናውን ላለማስነካትና ላለማስደፈር በምናደርገው ትግል ዓይነተኛ ውን ቦታ ይዞ ስለሚገኝ ብቻ ነው፡፡ “እንዴ! ታዲያ ዛሬ ምን አዲስ ነገር ተፈጥሮ ነው የእነርሱን ቆሻሻነት ማውሳት ያሰፈለገው?” የሚል ጉጉትን ያዘለ ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል፡፡ቢነሳም ሊያስደንቅ አይችልም፡፡ እኛም በበኩላችን ይኸን ዓይነት

ጥያቄ ቢነሳ፥ "ከንዑስ ከበርቴ" የሚመነጭ ሁሉን የማወቅ ማቋመጥ እንደሆነ ቆጥረን ዋጋ የምናሳጣው አይሆንም። ምክንያቱም፥ሕዝብ ማነኛውንም ጥያቄ ጠይቆ መልስ የማግኘት መብቱ መሠረታዊ መሆኑን አበክረን ስለምናምንበት ነው። እኛ ዛሬ የኢትዮጵያን ሕዝብ የአርበኝነትና የጀግንነት ታሪክ እንደገና እየተንሰራራና በየቦታውም እያበበ መምጣቱን ስንመለከት፥ የሀገራችን ትንሳዔ መቃረቡን እየተረዳን መምጣታችን፥ ወያኔዎች በሀገራችን ላይ የሰነዘሩትን ብሄራዊ ክብረ-ነክ ድምጥማጡን ለማጥፋት በሚደረገው የሀገራዊ ነፃነት ትግል የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉም ተባብሮ እንዲነሳ ብሔራዊ ጥሪ ለማስተላለፍ ነው። ለታሪክ ግንዛቤ ብቻ እንኳን ስንል፥ የወያኔ ዘረኞች በአንድ ወቅት የኢትዮጵያን ሕዝብ ያዋረዱበትን የባተሌ አነጋገር መጥቀስ እንፈልጋለን። በቋንቋቸው የተናገሩት ስንጠቅስ፥ በአንድ ወቅት እንዲህ ብለው ነበር፥

" እዚኦም እዱጋት፥ ስጋ ጥሬ መብልኣ ጥራይ ዕምበር ዝፈልጡ፥ ውግዕ
ዳ ኣበይ ኣዶም ይኽዕሉ "

ወደ አማርኛ ሲተረጎም የሚከተለውን የትዕቢት መልዕት ያስተላልፋል።

" እነኝህ አህዮች ጥሬ ስጋ መብላት ነው እንጅ የሚያውቁት ውጊያማ የት እናታቸውን ይችላሉ" የሚል ነው።

በራሳቸው ሀገርና ሕዝብ አኩሪ ታሪክ ላይ ይህንን የመሰለ አሳፋሪ መግለጫ ሲሰነዝሩ፥ ያተረፉት ነገር ቢኖር፥ የታሪክ መርገምን ብቻ ነው እንጅ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ተባብሮ ሀገሩን ከጥፋትና ከውርደት እንደሚያድናት ወደፊት የሚታይ ይሆናል።

ዛሬ፥ ማነኛቸውም የዓለም አቀፍ የፖለቲካ ተንታኞች፥ የኢኮኖሚ ጠበብቶች፥ የኢንተሊጀንስ/መረጃ ስብሰባ ባለሞያዎችና የምርምር ተቋማታ በአንድነት የሚስማሙበት ነገር ቢኖር፥ በሀገራችን ወደፊት ስለሚከሰተው አደገኛ ሁኔታ ላይ ነው። በአፍሪካ ውስጥ ከሱዳን ሌላ ሦስት ሀገሮች ብትንትናቸው ሳይወጣ አይቀርም ብለው "መርዶአቸውን" ያረዱላቸው ሀገሮች ናይጀሪያ፥ኢትዮጵያና ሶማሊያ

እንደሚሆኑ በማስረጃ የተደገፈ ትንታኔ ያቀርባሉ። እኛ ሀገራችን ስለገጠማት የህልውና አደጋ ከባዕዳን ማስጠንቀቂያ ያሻናል ለማለት ባንችልም፥ ችግሩ ከእኛ አልፎ ተርፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ የመነጋገሪያ ርዕስ መሆኑን ግን በአርምሞ ልንመለከተው አንችልም። ዞሮ ዞሮ ግን ሁላችንም ዜጎች፥ በአንድ፥ ማንም ሊያስተባብለው በማይችል ሀቅ ላይ ልንስማማ ይገባናል። ይኸውም፥ ለሀገራችን የወደፊት ክስመትና ጥፋት ሁላችንም ተጠያቂዎች መሆናችንን ነው። ከአንድ መቶ ዓመት በፊት በተመሳሳይ የታሪክ አጋጣሚ ምክንያት የተነገሩትን ሕዝባዊ እሮሮዎችና ዋይታዎች ጠቅሰን ሀተታችንን እንደመድማለን።

1. ባላቸውን ወንድማቸው ገድሎ በመሾሙ ሀዘንና ደስታ የተፈራረቀበትን ኅሊናቸውን ለማፅናናት ሲሉ አንድ የትግራይ ሴት ወይዘሮ እንጉርጉሮ አሰሙ ይባላል።

> “ የተሻረው ባሌ ተሿሚው ወንድሜ፥ አሁን ምን ልናገር ከሀዘን ላይ ቆሜ።”

ከአንድ መቶ ዓመት በኋላ ዛሬ የትግራይ ሕዝብ፥የሴት ወይዘሮዋን እንጉርጉሮ መልዕክት በደንብ ሊረዳው ይገባል። “ የምትጠፋው ሀገራችን፥ የሚያጠፏት ልጆቻችን” ብሎ መነሳት ይጠበቅበታል። ያለዚያ ከታሪክ ተጠያቂነት ሊያመልጥ አይችልም።

2. በአንድ ዘመን ነግሠው የነበሩትን ኃይለኛ መሪ ባኅርይ ለመግለፅ ሲባል ደግሞ ሕዝቡ የሚከተለውን አንጎራጎረ ይባላል።
“አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷቸው፥ተኩሶ አንገብግቦ አቃጥሎ ፈጃቸው”

በዚህ በዛሬው ትውልድ ዘመን ደግሞ፥ አፍኝ የማይሞሉ ጥቂት ዘረኞችን ማስወገድ አቅቶት፥ ብዛቱ ለቁጥር የሚያስቸግረው ተቃዋሚ ክፍል፥የሀገሪቱን መጥፋት የመጨረሻውን ምዕራፍ እያየ ቁልጭ ቁልጭ እያለ ተቀምጧል። ሁሉም ዜጋ ተባብሮ እነኝህን እኩይ ግለሰቦች ማስወገድ ካልተቻለው፥

ለሚቀጥለው ትውልድ ዋይታና ሰቆቃ ማስተላለፍ÷ኢትዮጵያን አያድናትም፡፡ አፍ የሚጎርሰውን እጅ ሊመጥነው ቢችልም፡፡ አፍ እንዳመጣ መናገር የኋላ ኋላ ማጠፊያው እንደሚቸግር÷ ውርድ ለራሴ እንላለን፡፡ በበኩላችን÷ እንድ ዜጋም እንደ ትውልድም የሚጠበቅብንን ከመፈፀም ወደኋላ አንልም፡፡ የሀገራችንን ኅልውና እስከ ታሪኳና ክብሯ ለማስጠበቅ ትግላችንን  እንቀጥል፡፡ ልብ ያለው ልብ ይበል! ልብ የሌለው ልብ ይግዛ!!!